# ሰርድሚል ተቋም
## የማስተማር/የስብከት ባጅ

*ከሙሴና ከነቢያት ሁሉ ጀምሮ በቅዱሳት መጻሕፍት ስለ እርሱ የተጻፈውን አስረዳቸው።*

ሉቃስ 24፡27

የመጽሐፍ ቅዱስን መልእክት በግልጽ እና በታማኝነት ማብራራት ስራ ይጠይቃል። በክፍል ውስጥ ተማሪዎች ፊት ወይም በመድረክ ላይ ብትቆምም፥ በማንኛውም ርዕስ ላይ ሰዎች ስለ መጽሐፍ ቅዱስ መልእክት ግልጽ በሆነ መንገድ መረዳት አለባቸው። ወደ ኤማሁስ በሚወስደው መንገድ ላይ፣ ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ ጊዜ ወስዶ ማንነቱን ገልጿል። ይህ ባጅ በዚህ ተግባር ላይ ብቻ ያተኩራል። አሰልጣኝህ መሪህ ሆኖህ ቅዱሳት መጻሕፍትን በታማኝነት ለማወጅ የማስተማርና የመስበክ ችሎታህን ለማዳበር እና ለማሳለጥ ጥረት ታደርጋለህ።

### ባጁ የሚያካትተው፡-

***ለምንባቡ ታማኝ*** - ምንባቡ የሚለውን ተናገር
***ለንዑስ ምንባብ ታማኝ*** - ትምህርትህ/ስብከትህ ኢየሱስንና ሥራውን እንዴት አድርጎ ይጠቁማል?
***ለአውድህ ታማኝ*** – ለአደማጮችህ በሚስማማ መልኩ ከመጽሐፍ ቅዱሳዊው ዓለም ድልድዩን ተሻግረህ ወዳለህበት ዓለም ተሻገር

### የውይይት ርዕሶች፡-

***ተግባራዊነት*** - በቤተ ክርስቲያንህ ወይም በአገልግሎትህ ውስጥ ማስተማር ወይም መስበክ ምን ይመስላል? ብዙውን ጊዜ የሚያስተምረው ወይም የሚሰብከው ማነው? በአብዛኛው ጊዜ ለምን ያህል ጊዜ ይቆያል?

**ጸሎት** - ምንባብ ስትመርጥ፣ ትምህርትህን ወይም ስብከትህን ስትዘጋጅ፣ ስታቀርብ እና መንፈስ ቅዱስን ለውጤቱ ስትታመን የጸሎት ሚና ምንድን ነው?

**እቅድ** - ምንባብ ወይም ርዕስ እንዴት መምረጥ አለብህ? ልታስተምር ከፈለከው ርዕስ ጋር የሚዛመዱት ምንባቦች የትኞቹ ናቸው?

**ክፍሎች** - ምንባቡ እንዴት ነው የተከፋፈለው? የምንባቡ ርዕሰ ጉዳይ ምንድን ነው? የምንባቡ ዋናው ነጥብ ምንነድነው? ደራሲው ዋናውን ነጥብ እንዲያግዝለት የተጠቀማቸው ነዑሳን ክፍሎች የትኞቹ ናቸው? ርዕሰ ጉዳዩን ለማብራራት የተጠቀሙት ዝርዝሮች ምንድናቸው?

**ተዘጋጅ** - በምንባቡ ውስጥ ግራ የሚያጋቡ ቃላት ወይም ሀረጎች አሉ? ጥቅም ስለሚኖራቸው ልታስረዳቸው የሚገቡህ ስሞች ወይም ቦታዎች አሉ? ይህንን ምንባብ ለማጥናት እንዲረዳህ ምን አይነት ምንጮች ሊኖሩህ ይገባል? ይህ ደራሲ ወይም ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ደራሲዎች ተመሳሳይ የሆነ ጭብጥ እንዴት ያዳብራሉ?

**ሰዎች** - አንተ የምታስተምርበት ወይም የምትሰብክበት ቡድን ውስጥ ምን አይነት ሰዎች አሉ?

**ዓላማ** - አንተ ከምታካፍለው ቃል የተነሳ የተለየ ውጤት እንዲኖር ተስፋ የምታደርገው ምንድን ነው?

**መከርከም** - ምን ዓይነት ምሳሌዎች/ሀሳቦች መቀመጥ አለባቸው? ምን መወገድ አለበት?

**ማምረት** - ትምህርትህን/ስብከትህን ጽፈህ ለአድማጮችህ ጽፈህ ብታነብ ይሻላል? ወይስ ጽፈኸው በቃልህ ብትይዘው ይሻላል? ወይም አጫጭር መግለጫ እና ማስታወሻ ማዘጋጀት ይሻላል?

**ተለማመድ** - ትምህርቱን/ስብከቱን ከማቅረብህ በፊት መለማመድ ያስፈልግሃል? የት ትለማመዳለህ? እንዴት ልትለማመድ ተችላለህ? ከተለማመድክ በኋላ፥ ማስተካከል/መለወጥ ያለብህ ነገር ይኖራል?

**አመልክት** - በሉቃስ 24፡27 ኢየሱስ ወደ ኤማሁስ በሚወስደው መንገድ ላይ፥ ሁሉም ቅዱሳት መጻሕፍት ወደ እሱን እንዴት እንደሚያመለክቱ አሳይቷል። ትምህርትህ/ስብከትህ ወደ ኢየሱስ እንዴት ይጠቁማል?

**ፍጥነት** ስትናገር ትፈጠናለህ፣ ትዘገያለህ፣ ወይስ ብዙም ለውጥ ሳይኖር በተመሳሳይ ፍጥነት ትናገራለህ?

**አቅርብ** -አድማጮችህ ሲሄዱ ሊያስቡበት ወይም ሊያደርጉት የሚችሉ የሰጠሃቸው ነገር አለ?

**አሰላስል** - አድማጮችህ ለኢየሱስ ብቻ በሚኖራቸው ፍቅር እና መሰጠት ይነሳሳሉ?

**ኃይል** – ትምህርትን/ስብከትን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በማቅረብ እና በራስህ ጥንካሬ በማቅረብ ላይ ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

## ወደ ተግባራዊነት፡-

1. በአሰልጣኝዎ በተሰጣችሁ ቅደም ተከተል በመከተል አንድ ትምህርት/ስብከት በማዘጋጀት በቡድንዎ ውስጥ ላሉ ሰዎች አቅርቡ።

2. ለአስተያየት የሚከተሉትን ጥያቄዎች ጠይቁ፡-
   ግልጽ የሆነላችሁ ምን እና ምን ናቸው? ግልጽ ያልሆነው ምንድነው?
   ከትምህርቱ/ስብከቱ በጣም የተስማማኸው ከምን ጋር ነበር?
   እነዚህ ሐሳቦች በሕይወቴ ውስጥ ምን ለውጥ ሊያመጡ ይችላሉ?
   ይህ ትምህርት/ስብከት ለኢየሱስ ያለኝን ፍቅር አነሳስቷል?

3. በአጥቢያችሁ ቤተ ክርስቲያን ይህንኑ ትምህርት/ስብከት አቅርቡ።

## የባጅ መስፈርት፡-

ይህ ባጅ ***ወደ ተግባራዊነት*** የሚለውን የትምህርት ክፍል ከ ***ባጅ አካላት*** እና ***ለውይይት ከቀረቡት ርዕሶች*** አንጻር በታማኝነት እና ባለማቋረጥ በተሳካ ሁኔታ ኮርሱን በሙሉ ሲያጠናቅቅ በአሰልጣኙ ይሸለማል።